የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፱
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.59
ADDIS ABABA 25th April, 2019

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፶/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………..………ገጽ ፲፩ሺ፪፻፵

## Content

Regulation No. 450/2019

Driver's Qualification Certification License and Related Services Fee Regulation …..Page 11240

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፶/፪ሺ፲፩

### የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፭ እና በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፬/፪ሺ፲ አንቀጽ ፳፰(፩) መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 450/2019

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR DRIVER'S QUALIFICATION CERTIFICATION LICENSE AND RELATED SERVICES FEE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1097/2018 and Article 28(1) of the Driver's Qualification Certification License Proclamation No. 1074/2018.

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፶/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Driver's Qualification Certification License and Related Services Fee Regulation No. 450/2019."

**፪. ክፍያ**

በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፬/፪ሺ፲ መሠረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠትና ተያያዥነት ላላቸው አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

**2. Fee**

Fees to be charged for the issuance of driver's qualification certification license and related service pursuant to the Driver's Qualification Certificate License Proclamation No.1074/2018 shall be as prescribed in the Schedule attached hereto.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፫. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>**

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፷፪/፪ሺ፬ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

**፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**3. <u>Repealed Law</u>**

Driver's Qualification Certification License Fee Council of Ministers Regulation No.262/2012 is here by repealed.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall come in to force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 25th day of April, 2019.**

**ABIY AHMED (PHD)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA.**

## የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያ ሠንጠረዥ

| ተራ ቁ. | የአገልግሎት ዓይነት | ክፍያ (ብር) |
|---|---|---|
| ፩ | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ(ለሁሉም ምድብ) | ፮፻፹ |
| ፪ | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ዕድሳት፣ምትክ ወይም ኢንተርናሽናል መንጃ ፈቃድ (ለሁሉም ምድብ) | ፮፻፷ |
| ፫ | ለአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ወይም የራሳቸውን ሠራተኞች ለሚያሰለጥኑ ሌሎች ተቋማት አዲስ ወይም ምትክ ፈቃድ ሲሰጥ | ፭ሺ፩፻፸፭ |
| ፬ | ለአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋም ወይም የራሳቸውን ሠራተኞች ለሚያሰለጥኑ ሌሎች ተቋማት ፈቃድ ሲታደስ | ፪ሺ፭፻፸ |
| ፭ | ለቴክኒሽያን አዲስ ወይም ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ወይም ጊዜያዊ የማሠልጠን ፈቃድ ሲሰጥ | ፬፻፵፭ |
| ፮ | ለቴክኒሽያን የብቃት ማረጋገጫ ሲታደስ | ፫፻፵ |

Schedule of Fee for Driver's Qualification Certification
License and Related Services

| NO | Type of Service | Fee |
|---|---|---|
| 1 | Issuance of new driver's qualification certification license (for all categories) | 680 |
| 2 | Renewal or Replacement of driver's qualification certification license and international driving license (For all categories) | 620 |
| 3 | Issuance or Replacement of license for driver's training institution or for other institutions that train their employees | 5,175 |
| 4 | Renewal of license for driver's training institution or others institution or for others institution that train their employees. | 2,570 |
| 5 | Issuance or Replacement of certification of competence for Technician or issuance of temporary training license | 435 |
| 6 | Renewal of certificate of competence for technician | 330 |